# ቀስተ ደመና

የሰላምና የወድማማችነት ድምፅ ሬድዮ ጋዜጣ

ቁጥር 4-6

ታህሣሥ / የካቲት 1990

## ከአዘጋጅ ብዕር

የቀስተ ደመና ሬዲዮ፤ የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ ሥርጭቱን የጀመረው መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ ም ነው።

ይህ ሁለተኛ መጽሄት የሚቀርበው ሬዲዮው ከጀመረ ከስድስተኛው ወር በኋላ ስለሆነ በቅርቡ ከተላለፉትና ባጭሩ ከቀረቡት የተወሰኑ ዜናዎች ሌላ፤ የመጽሄቱ ዋና ይዘት ለሃገራችን ወቅታዊ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ቅድሚያ ትኩረት ለሰጡ ትችቶች፤ ትንተናዎች ወዘተ ነው።

መልካም ንባብ !

* ክሊንተን አፍሪካ........................1
* የፖለቲካ አጥቂነት....................2
* በአንድ ራስ አንድ ምላስ.........3
* ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ኬንያ.......5
* የእብዶች ሎጂክ .......................6
* በ 1992ቱ ምርጫ ላይ የተጠነሰሰው ሤራ....................7
* ህወሀት ለምርጫ ይዘጋጃል፤ ተቃዋሚዎችስ?.........................8
* የወያኔ መሰንበቻ ስልት...........10
* ከጋዜጦች አምድ.................... 11
* ዘመናዊ ባርነት...................... 15
* የወያኔን ኢትዮጵያ ሾላ በድፍን........................17

ቀስተ ደመና (Radio Rainbow) የሰላምና የውንድማማችነት ድምፅ ሬዲዮ
በአጭር ሞገድ(short wave) እንደሚከተለው ይተላለፋል ፤

| ቀን | ሞገድ | ሰዓት | አቅጣጫ |
|---|---|---|---|
| ሐሙስ | 19 ሜትር ባንድ<br>15.365HZ | በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር<br>ከምሽቱ 1 እስከ 2 ሰዓት | ምስራቅ አፍሪካ<br>ኢትዮጵያ |
| ዓርብ | 31 ሜትር ባንድ<br>9855kHz | በአሜሪካ ሰዓት አቆጣጠር<br>9.00p.m. - 10.00pm | ሰሜን አሜሪካ<br>ምስራቃዊ ጠረፍ |
| እሁድ | 49 ሜትር ባንድ<br>5.910kHz | በአውሮፓ ሰዓት አቆጣጠር<br>9.00a.m-10.00am (10.00-11.00a.m ለብሪታንያ ) | ምዕራብ አውሮፓ |

አድራሻችን፤
አስተያየት፤
ትችት፤ ወዘተ
ካላችሁ,

Radio Rainbow ,
c/o P.O .Box 140104
53056 Bonn , Germany
Fax : 0049 228 612381

GRAPECA ሰኢአቀ RAGPEHA
Groupe de Recherche et d'Action pour la paix en Ethiopie et dans la Corne de l' Afrique
Research and Action Group for peace in Ethiopia and the Horn of Africa
ሰላም ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን

ቁጭታቸውን ለመወጣት በዚያውም በእራሳቸው "ታጋይ" ሴቶች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን አለ ተፎካካሪና ተጋሪ ለመሙላት ሃሳብ አላቸው የሚሉትም የዚያኑ ያህል ብዙ ናቸው። "የመሃል አገሩን ሕዝብ ቁጥር በዚህ ሥራችን" "እንቀንሰዋለን" ብሉ መገመት አላማ እንደሆነም ብዙዎቹ ይናገራሉ።

ትናንት እንደተጻፈባቸው፤ ፈላሻዎችን ከኢትዮጵያ በማስወጣት ሥራቸው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር የተቀበሉት ወያኔዎች፤ የኢትዮጵያ ሴቶች ወደ አረብ አገር በመሸጥ ምን ያህል ብር እስካሁን ድረስ ገቢ እንዳደረጉ ምንም የሚታወቅ ነገር የለም። ግን "ወላጆች ፤ ወንድሞቸቸው ይህን አይነቱን ነገር የሚያጋልጡበት ፤ በአደባባይም የሚቃወሚበት፤ ......ቀን እሩቅ አይሆን ይሆናል" ብለው አንድ በመካከለኛው ምሥራቅ ፤ በአውሮፓና፤ በአሜሪካ፤ እየተዘዋወሩ የእግዚአብሄርን ቃል የሚያስተምሩ የሃይማኖት አባት "ትንቢት" አዘል ግምታቸውን ለምያዳምጡት አሰምተዋል።

**ሌሎቹ ከዚህ "ባርነት" አይሉት "ሥራ" "ንግድ" አይሉት ሕዝብን አውቆ በሕጋዊ መንገድ "ማባረር" ምኑም ያልታወቀውን ተንኮል "ዝም ብላችሁ አትዩ" ብለው ተጣርተዋል።**

ለሴቶች መብት ፤ እኩልነት፤ የቆመም ይህንን ጥሪ ዝም ብሉ አይቶ ማለፍ አይችልም። ብለው አስተያየታቸውን ደጋግመዋል።

-------- ////--------

## የወያኔን ኢትዮጵያ ሾላ በድፍን

ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር በ 1970 ዓ ም አፍሪካን ከጎበኙ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሌላ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ይችን አህጉር በመጎብኘት ላይ ናቸው። ቀደም ሲል ይጎበኛሉ ከተባሉት አገሮች መሃከል ኢትዮጵያ ተሰርዛለች። ከብዙ አቅጣቻዎች ለዚህ የፕሬዚዳንት ክሊንተን የጉዞ ፕላን ለውጥ የተለያዩ ምክንያቶች ይሰነዘራሉ። በሃገሪቱ ያለው ያለመረጋጋት ሁኔታና የወያኔ መንግሥት ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ያለበት ችግር የፕሬዚዳንቱን አማካሪዎች ስጋት ላይ ስለጣላቸው ነው የሚሉ ታዛቢዎች አሉ። ሌሎች ደግሞ ፕሬዚዳንቱ ይጎበኟቸዋል ከተባሉት አገሮች የአንዳቸውም ዜጎች ይህንን ጉብኝት በይፋ ሰልፎች ሳይቃወሙ ኢትዮጵያውን በብዙ የምዕራብ አገሮች በተቃውሞ ሰልፍ ድምጻቸውን ማሰማታቸውና ይህ አልበቃ ካለ አዲስ አበባ ከደረሱ ከፍተኛ ሰልፍ ይጠብቃቸዋል ተብሉ የተሰነዘረው ዛቻ ስላሰጋቸው ነው የሚሉ አሉ። በእርግጥም እነዚህ ምክንያቶች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረጋቸው አይካድም። ነገር ግን ጉዳዩን ጠለቅ ብለን ስናየው የዚህ ጉብኝት መሰረዝ መሠረታዊ ምክንያት በወያኔ+ኢህአደግ ኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ የፕሬዚዳንቱን ዓላማዎች የሚጻረር መሆኑን እንረዳለን።

ፕሬዚዳንት ክሊንተን አፍሪካን በሚጎበኙባቸው 12 ቀናት እግራቸው የረገጣቸው አገሮች ሁሉ በምዕራብ አገሮችም ሆነ በተለይ ደግሞ በአሜሪካ የመገናኛ ብዙሃንን ትኩረት የሚስቡ አገሮች እንደሚሆኑ ግልጽ ነው። እንድያውም የፕሬዚዳንቱ ጉዞ አንዱ አላማ ራሳቸው "አዲሲቱ አፍሪካ" ብለው በሰየሟት አህጉር የአሜሪካን ህዝብ ይበልጥ ግንዛቤ እንድያገኝ እንደሆነ ግልጽ ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ ኢትዮጵያ አንዲትም ሆነ ሁለት ቀናት በዚህ ጉብኝት ሳቢያ አትኩሮት ብታገኝ ፕሬዚዳንቱ ስለአዲሲቱ አፍሪካም ሆነ በዚች አዲስ አህጉር አሜሪካ ትጫወታለች የሚሉትን አወንታዊ ሚና ለመስጠት የሚሞክሩትን ስእል እንዳያበላሽባቸው መስጋታቸው ግልጽ ነው።

ፕሬዚዳንቱ ገና ስለጉዝዋቸው ከመጀመሪያው መግለጫ ሲሰጡ "ከወር ወር በደሞክራሲ ሥር መሰደድም ሆነ በሰው ልጅ መብት መከበር ፤ እንዲሁም በኢኮኖሚ ልማትና እድገት አስደናቂ እርምጃ በማድረግ ላይ ያለችውን አዲሲቱን አፍሪካ እጎበኛለሁ" ተናግረው ነበር። እንዲህ አይነቷን አዲስ አፍሪካ ራሳቸውም በገዛ ዓይናቸው ለማየትም ሆነ

ለአሜሪካንም ሕዝብ ለማስተዋወቅ ሲነሱ ፕሬዚዳንቱ ተሽቀዳድመውና ተቻኩለው ኢትዮጵያን ከተጎብኝ አገሮች እንደጨመሯት ቢሄዱ ኖሮ ይቺ አገር ከ 10ሺ በላይ የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ ከአፍሪካ አንደኛ እንዳደረጋት ሲገለጥ፤ እስር ላይ በሚማቅቁት ጋዜጠኞች ብዛት በዓለም ከቻይና ቀጥላ ሁለተኛ መሆኗ ይፋ ሲወጣ ምን ሊባል ነበር? ዜጎች በጠራራ ፀሀይ በጥይት ይደበደባሉ ተብሎ በጋዜጦች ሲጻፍ ፕሬዚዳንት ክሊንተን በምን ተአምር በሰው ልጅ መብት ማክበር ይቺን አገር እንዴት በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላቸው ነበር?

ሁለተኛና ለዚህ ጉብኝት የተሰጠው ምክንያት ወይም ዓላማ ኢኮኖሚያዊ ነበር። በዋሺንግቶን ከተማ የሚገኘው "ሴንተር ፎር ስትራተጂክ ኤንድ ኢንተርናሽናል ስተዲስ" የአፍሪካ ክፍል ሃላፊ ወይዘሮ ኮንስታንቲን ፍሪማን በዚህ ጉዳይ ሲጽፉ የፕሬዚዳንቱ ጉዞ 700 ሚሊዮን የወደፊት ደንበኞች ያሉበትን አህጉር ለመጎብኘት ሲሆን "ቀደም ሲል ፈረንሳዮችና እንግሊዞች አፍሪካ ሀብት ሊዛቅ የሚቻልበት አህጉር መሆኗን እንደደረሱበት ሁሉ የአሜሪካን ነጋዴዎችና ባለሃብቶች ይህንን ሃቅ እንዲገነዘቡ ይገባል" በማለት አብራርተዋል። ነገር ግን ይህ ሀብት ሊዛቅ፤ ንግድ የማስፋፋትና ገበያ የማድራት ዓላማም ቢሆን ከሁሉ አስቀድሞ የተረጋጋን ሁኔታ ይጠይቃል። የነወያኔ ኢትዮጵያ በፕሬዚዳንቱ ጉብኝት ሳቢያ መገናኛ ብዙሃን ዓይን ብትገባ ኖሮ፤ እርግጥ የተፈጥሮ ሃብቷ እንደዚሁም ደግሞ ለመጎብኘት ከታጩት 6 አገሮች የአምስቱ ቢደመር በህዝብ ብዛት የኢትዮጵያን የማያክል መሆኑ ሲታወቅ አስጎምጂ አገር ትሆን ነበር። ግን እዝያው በዚያው ደግሞ በሃገሪቱ የሰፈነው የአለመርጋጋት ሁኔታ ለአሜሪካኖች የኢኮኖሚ ዓላማ የማትመች አገር መሆኗ ይጋለጥ ነበር።

ሶስተኛውና እኚሁ ወይዘሮ ፍሪማን የጠቀሱት ዓላማ የአሜሪካንን የራሷን የውስጥ ፖለቲካ የሚመለከት ነው። ባጭሩ አሜሪካዊቷ ምሁር የሚሉት ፕሬዚዳንቱ በዚህ ጉብኝታቸው የሚፈልጉት ለአፍሪካ ልማትና ዴሞክራሲ ተቆርቋሪ መሆናቸውን፤ ለጥቁር አሜሪካውያን በግልጽ በማሳየት የነዚህን ዜጎች ድጋፍ ለሳቸውና ለፓርቲያቸው ለማግኘት እንደሆነ ይገልጻሉ። ፕሬዚዳንቱ ይህንን ዓላማ ለማሳካት ይችሉ የነበር የሰው ልጅ መብቶች የሚከበሩባት፤ በጸጥታና በተረጋጋ ሁኔታ የእድገትና የልማት ሥራዎች የሚካሄድባት ሀገር በማሳየት ብቻ ሳይሆን ለዚህ በጎ ሂደት አስተዳደራቸው አደረገ የሚሉት የጎላ አስተዋጽኦ ማሳየት ቢችሉ ነበር። ግን ይህም የሚያዋጣ አልሆነም። የወያኔ ኢትዮጵያ ጉዳይ የአንድ ሰ ሞን ከፍተኛ ዜና ቢሆን ኖሮ ጎልቶ የሚታየው የዚች አገር አሳዛኝ ሁኔታ ብቻ አልነበረም። የአሜሪካን መንግሥት በሃገራችን ሥር እየሰደደ ለሚሄደው አረመኔ አገዛዝ እውር ድጋፍ በመለገስ የሚጫወተውም ሚና አብሮ ይጋለጥ እንደነበር ግልጽ ነው። በአጭሩ የአሜሪካን አስተዳደር በዚህ ፕሬዚዳንታዊ ጉብኝት ሳቢያ የኢትዮጵያ ሁኔታ ትኩረት ቢያገኝ የአዲሱ ደሞክራሲያዊት አፍሪካን ገጽታ ሳይሆን ከዚህ በጎ ሂደት ተነጥላ በጨለማ ውስጥ የምትዳክር፤ ላለመረጋጋትና ለትርምስ ደረቷን የሰጠች አገር በመጎብኘትና በመደገፍ ላይ እንዳሉ የሚጋለጥ ጉብኝት ይሆን ነበር ማለት ነው። ይህም በመሆኑ ከሴኔጋል እስከ ደቡብ አፍሪካ ሲዘዋወሩ ፕሬዚዳንቱ አሳብረው ኢትዮጵያን አልፈው ሲሄዱ "የወያኔ ኢትዮጵያ ነገር ሾላ በድፍን" የሚል ምርጫ ያደረጉ ይመስላል።

**እሳቸው ያሉትን ይበሉ መብታቸው ነው። እኛ ግን በዚሁ በዛሬው የዜና የጠቀስናቸው ኮፊ አናን ሰብአዊ መብት ሲባል እኛንም ይጠቅሰናልና፤ ልጆቻቸው በአደባባይ በጥይት ሲደበደቡ እናቶች የሚያነቡት እንባ ይመለከተናልና፤ በሃገራችን በመፈጸም ላይ ያለው ግፍ፤ የኢህአዴግ የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ በማመቻቸት ላይ ያለው የህዝቦች የእርስ በርስ ግጭት ይመለከተናልና የኢትዮጵያ ጉዳይ ሾላ በድፍን ብለን ለማለፍ አንችልም። ፕሬዚዳንት ክሊንተን የሚሏትን አዲስ አፍሪካ ለአፍሪካ የሚያመጡላት ፕሬዚዳንት ክሊንተን አይደሉም። እኛው በትግላችንና በመስዋእትነታችን እንጂ።**

-------- ////--------